አማኞች ጀነት ውስጥ ከአንድ ወጥና ውስጡ ባዶ ከሆነ ሉል የተሰራ ድንኳን አላቸው። ርዝማኔውም ስልሳ ማይል ነው። ለአማኞችም በውስጡ ሚስቶች አሏቸው። አንድ አማኝ እነርሱን (ሊገናኝ) ይዞራል። ነገር ግን እርስበርሳቸው አይተያዩም።

ከአቡ ሙሳ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው: ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብለዋል: "አማኞች ጀነት ውስጥ ከአንድ ወጥና ውስጡ ባዶ ከሆነ ሉል የተሰራ ድንኳን አላቸው። ርዝማኔውም ስልሳ ማይል ነው።
ለአማኞችም በውስጡ ሚስቶች አሏቸው። አንድ አማኝ እነርሱን (ሊገናኝ) ይዞራል። ነገር ግን እርስበርሳቸው አይተያዩም።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ስለአንዳንድ የጀነት ፀጋዎች ተናገሩ። ጀነት ውስጥ ለአማኞች ትልቅና ውስጡ ሰፊ የሆነ ከአንድ ውስጡ ባዶ ከሆነ ወጥ ሉል ድንኳን ተዘጋጅቶላቸዋል። ወደ ሰማይ አግድመቱና ርዝመቱ ስልሳ ማይል የሚሆን ነው። ከአራት ማዕዘን ጎኖቹ መካከል በየሁሉም ጎንና ጥግ ሚስቶች አሉት። አንዳቸው ከአንዳቸው ጋር አይተያዩም። አማኙም በመካከላቸው ለግንኙነት ይዞራል።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/8349